# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 8 ቁጥር 5 ነሐሴ 28 ቀን 2013 ዓ.ም.

## ኢሕአፓ የትግል ዓላማ ነው

*ኢሕአፓ ለሕዝብ ይፋ የሆነበትን 46ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀ*



በቅድሚያ ዘላለማዊና ትውልድ ተሻጋሪ ትዝታዎችን፣ ሙዚቃዎችን ለየት ባለ አቀራረብና አዘፋፈን ስልቱ በድምጹ ትቶልን፣ በትላንትናው ዕለት ከዚህ ዓለም በሞት ለተለየው ታዋቂው ድምፃዊ አለማየሁ እሸቴ የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን ለመላው ቤተሰቡ፣ ዘመድ ወዳጆቹ፣ አፍቃሪ ጓደኞቹና ለመላው ሕዝብ እንገልፃለን።

***ለመላው የኢትዮጵያ ወገኖቻችን፦***

ነሐሴ 26 ቀን በ1967 ዓ.ም. እራሱን ለሕዝብ ይፋ ላደረገው ኢሕአፓ 46ኛ ዓመት እንኳን አደረሳችሁ መልዕክታችንን እናቀርባለን። ትግል ሕዝባዊ ዓላማ መሆኑን በተግባር ያሳየው ኢሕአፓ ለሀገራችን ኢትዮጵያ እና ለሕዝባችን አመቺ ያለውን ማታገያ ፕሮግራሙን ይፋ አድርጎ ተቀላቀሉኝ ሕዝባዊ ጥሪውን ልክ የዛሬ 46 ዓመት አቀረበ። የኢሕአፓ 1967 ዓ.ም. የሕዝባዊ መንግሥት ምስረታ ማታገያ ፕሮግራም በማቅረብ በሀገራችን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበረሰባዊ ጉዳዮች ላይ ያለውን አቋም ያሳወቀበት ጥቅል ፕሮግራሙ በዘጠኝ ክፍሎች የተብራራ ባለ 31 ገጽ ጥራዝ ነበር።

(http://yatewlid.com/images/PDF/PoleticalProgram/EPRP_Program_Nehase_1967.pdf )

ትግሉ ዘር፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ፆታ፣ ዕድሜ ሳይለይ ሁሉንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቅፍ ዘንድ ***"የኢትዮጵያ"*** ብሎ የተነሳ፣ ለሕዝብ ይፋ ያደረገው ማታገያ ፕሮግራሙ የሀገሪቷንና ሕዝቡን መሠረታዊ ጉዳዮች የዳሰሰ በመሆኑና ወገንተኛነቱ ለሕዝብ መሆኑን ለማሳወቅ ***"ሕዝባዊ"*** ነኝ ያለ፣ ለተሸራረፈ ጥገናዊ ለውጥ ሳይሆን ለሕዝብና ሀገር ይበጃል ያለውን ሥር-ነቀል ለውጥ ለማምጣት ***"አብዮታዊ"*** ብሎ እና እራሱን በሁሉም የሀገሪቷ ክፍል ሲያዋቅርና ሲያሰባስብ ቅድመ እንቅስቃሴዎችን አካሂዶ ***"ፓርቲ"*** የመሆን ብቃቱን ገምግሞ ***"የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ"*** ብሎ በሀገራችን ብቅ ያለ የመጀመሪያው የፖለቲካ ፓርቲ ነበር። በወቅቱ በወጣው ፕሮግራም እራሱን ሲያስተዋውቅ ፤ *"የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ሦስት ዓመት ተኩል በሕቡዕ/ድብቅ/ ከታገለ በኋላ ድርጅታዊ አቅዋሙን አስተካክሎና ኃይሉን አጠናክሮ ለዚሁ ዓላማ ለመታገል ታጥቆ መጥቶአል።"* ገጽ 6፡ ነበር ያለው ልክ የዛሬ 46 ዓመት።

ኢሕአፓ ምን ዓይነት ፓርቲ እንደነበር እራሱን ሲያስተዋውቅ *"የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የላብ-አደር መደብ ፓርቲ ነው። ዓላማው የላብ-አደሩንና የአርሶ-አደሩን አንድነት ለማጠንከርና የላብ-አደር መደብ ዲክታተርሺፕ /ፍጹም ሥልጣን/ ለመመሥረት በዚህም አማካይነት አንድ ሰው በምንም ዓይነት ሌላውን ሰው የማይበዘብዝበት፣ ሕብረ-ተሰብ ያፈራው ሀብት ለመላው ሕብረ-ተሰብ ጥቅም የሚውልበት ማንኛውም ዓይነት ጭቆና የማይታወቅበት፣ ለሕብረ-ተሰቡና ግለ-ነፃና ጠቅላላ እድገት ዋስትና የሚገኝበት መደብ አልባ ሕብረ-ተሰብን መገንባት ነው።"* ገጽ 3፡ በሚል ነበር ልክ የዛሬ 46 ዓመት ማታገያ ፕሮግራሙን ለሕዝብ ይፋ ያደረገው።

ኢሕአፓ በፕሮግራሙ ገጽ 4 ላይ የየካቲት 1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ አብዮት አቅጣጫውን እየሳተ በመምጣቱ ሰፊው ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት ሚናውን በማጣቱና ስለ ምጣኔ ሀብት ይዞታ በወቅቱ አቋሙን ሲገልጽ *"ሰፊው ሕዝብ በጊዜ በቂ ስፋትና ተሰሚነት ያለው አቀነባባሪ ግንባር ቀደም ፓርቲ ድርጅት በማጣቱ የመንግሥት ሥልጣን የጨበጠው የምርጥ መኮንኖች መንግሥት ፖለቲካና ኢኮኖሚን በመነጣጠል በኢኮኖሚ በኩል አንዳንድ መሠረታውያን እርምጃዎችን ሲያውጅ በፖለቲካ በኩል ግን ሰፊውን ሕዝብ የዲሞክራሲያውያን መብቶችን ነስቶ የግሉ አምባገነናዊነት አቋቁሟል።"* በሚል ግልጽ ቋንቋ ነበር ያስቀመጠው።

ኢሕአፓ ገና ከጅምሩ ስለ ግንባር አስፈላጊነት ሲገልጽ ከፕሮግራሙ እንጥቀስና *“. . . የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ አዲሱ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን እግቡ ለማድረስ ከሚታገሉት ኃይሎች ሁሉ የያንዳንዱ ፓርቲ ወይም ቡድን የመደራጀትና የማስተማር ነፃነት እስከተጠበቀ ድረስ በአንድ የጋራ ግንባርም በመተባበር ለመታገል ዝግጁ ነው።”* ገጽ 6፡ ይህም ሥልጣን ለብቻዬ ልጠቅልል ሳይሆን በጋራ ለሀገርና ለሕዝብ መታገልና መምከር እንደሚያስፈልግ ሲጠቁም ነበር።

ኢሕአፓ ስለ ዴሞክራሲያ መብትና ስለ ሕዝቡ የስልጣን ባለቤትነት ግብ መድረስ ለመታገል ቆርጦ የተነሳ ፓርቲ መሆኑን በፕሮግራሙ ገጽ 6 መጨረሻ ላይ ሲያበስር *“የኢትዮጵያ ላብ-አደር በጠቅላላው ሰፊው ሕዝብ ከእንግዲህ ወዲህ ከየትም በማንም ስም በመጣ ጭቆናንና ብዝበዛን ለመሸከም አይችልም። አንተ የሚበጅህን አታውቅም፣ እኔ አውቅልሀለሁ የሚል ሞግዚት አይፈልግም። ጠመንጃ ያዘለ ይግዛህ የሚል ፈሊጥ አይቀበልም። የዲሞክራሲያዊ መብቶቹ ከተጠበቁለት በዲሞክራሲያዊ መንገድ ይታገላል፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ከተነፈገም አብዮቱ ግቡን እንዲመታ አስፈላጊ የሚሆኑትን የትግል ዘዴዎች ሁሉ ይጠቀማል። . . .”* በማለት ነበር ትግል ማለት ዓላማና ጽናት እንደሆነ ከጅምሩ አድምጡኝ፣ አንብቡኝ፣ ተመልከቱኝ ያለው።

በመጨረሻም ለላብ-አደሩ ለአርሶ-አደሩና ለሠፊው ሕዝብ በተላለፈው የትግል ሕዝባዊ ጥሪ መሠረት የነሐሴ 1967 ዓ.ም. የፓርቲው የእወጃ ፕሮግራም በዚህ መልኩ ነበር የተቋጨው *“ሰፊው ሕዝብ ሆይ! የስንት ዓመታት ጭቆና እንዲያበቃ፣ ብዝበዛ እንዲያከትም አምና በየካቲት “በቃኝ፣ በቃኝ፣ አንገፈገፈኝ” ብለህ ተነሳህ። . . . ግን ጭቆናው በከፋ መልክ፣ ብዝበዛው በረቀቀ ዘዴ ይቀጥላል። ነገሩ ግልጽ ነው። የድካምህ ፍሬ፣ የሲጋህ ቁራጭ፣ የአጥንትህ ፍላጭ የሆነው ልጅህን - አብዮቱን - በሞግዚት ሰበብ አምባገነን የእንጀራ አባት ቀማህ። አብዮት በጉልበተኛ እንጀራ አባት እጅ እየቆረቆዘ፣ ማንነቱን እየሳተ፣ ወላጁን እየካደ ያንተው አጥፊ በመሆን ላይ ነው። ስለዚህ ሳይዘገይ፣ በጊዜው የአብዮቱ ወላጅ መሆንክን አሁኑኑ አስመስክር፣ የወላጅ መብትህን አስከብር። ልጅህን ራስህ አሳድግ፣ ለቁም ነገር አብቃው፣ ስለሆንም ከአምባገነኖች እጅ በጉልበትህ ቀምተህ ተረከበው። በዚህ ታሪካዊ ትግልህ ኢ.ሕ.አ.ፓ. ጠበቃህ ሆኖ ከጎንህ ቆሞልሃል።”* ገጽ 30፡ የኢሕአፓ የነሐሴ 1967 ዓ.ም. ፕሮግራም።

**የዛሬ 46 ዓመት ነሐሴ 26 ቀን 1967 ዓ.ም. በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በትግሪኛ ቋንቋ ለኢትዮጵያና ልጆቿ የተሠራጨው የኢሕአፓ ፕሮግራም በተጨማሪ በእንግሊዘኛ፣ ፈረንሳይኛና አረብኛ ቋንቋ ተሰራጭቷል።**

ኢሕአፓ የዛሬ 46 ዓመት እራሱን ለሕዝብ ይፋ ሲያደርግ በዚህ መልኩ ቃል ኪዳን ገብቶ፣ “ፍፁም ነው እምነቴ፡ የትግሉ ነው ሕይወቴ” ዘምሮ ነበር ለሕዝብ ቀርቦ ከሕዝብ የተቀላቀለው። ታሪክ ነውና ጥንስስ ፕሮግራሙን በመጠኑ ለማስተዋወቅ ሞክረናል። ይህ የዛሬ 46 ዓመት ብቅ ብሎ በአቀረበው በዚህ መሪ ፕሮግራሙ መሠረት እጅግ በአጭር ጊዜ ከምዕራብ ምሥራቅ፣ ከደቡብ ሰሜን እጆቹን ዘርግቶ የታቀፈ ፓርቲ፤ ወጣቱን፣ ላብ አደሩን፣ አርሶ አደሩን፣ ሠራተኛውን፣ መምህራንን፣ ሴቶች እህቶቻችንን፣ ወታደሩን በአንድ ዓላማ ያሰለፈና ትግል ማለት ምን እንደነበር ያስመዘገበ ፓርቲ እናስታውሰው ዘንድ ግድ ይለናል። ትግል ማለት ሕዝባዊ ዓላማ መሆኑን በፕሮግራሙ፣ ትግል ማለት ጽናት መሆኑን ሳያወላውሉ በታገሉ አባላቱ፣ ትግል ማለት መስዋእትነት መሆኑን “በትግል መሞት ሕይወት” ባሉ ልጆቹ፣ ትግል ማለት እምነት መሆኑን “ፍጹም ነው እምነቴ፡ የትግሉ ነው ሕይወቴ” እያሉ ባንደበታቸው በዘመሩ ታጋዮቹ አስመስክሯል። ኢሕአፓ አመራር አካላቱ ሳይታወቁ ወጣቱንና ሕዝቡን ያንቀሳቀሰው በነሐሴ 1967 ፕሮግራሙ ነበርና ነው **ኢሕአፓ የትግል ዓላማ ነው** የምንለው።

ኢሕአፓ እና ያሰለፋቸው አባላቱና ሕዝቡ ለሕዝባዊ መንግስት ምስረታ እና ገደብ ለሌለው ዴሞክራሲያዊ መብት ድል ባይበቁም በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ከፍተኛውን ድርሻ እንዳስመዘገቡ የሚካድ ሀቅ አይደለም። ያ ትውልድ ለሀገሩና ለሕዝቡ የነበረው ቀና መንፈስ ሲወሳ እንኳን አፍቃሪ ወገኖቹ ይቅርና ጠላቶችም ኢሕአፓን ሳይጠቅሱ የማያልፉት የታሪኩ እምብርት ስለነበር ነው። በሕይወት ላላችሁ የኢሕአፓ አባላት፣ ደጋፊዎችና ያ ትውልድ አካላት እንኳዋን ለአርባ ስድስተኛው የኢሕአፓ ምስረታ አደረሳችሁ እያልን ለተሰዉና በሕይወት ለሌሉም ሰማዕታት ትግላችሁ ህያው ነው እንላለን።

*"ያ ትውልድ ተቋም"* ኢሕአፓ እራሱን ለሕዝብ ይፋ ያደረገበትን 46ኛ ዓመት ስንዘክር በኢሕአፓ እና በያትውልድ ዘመን የተዘገቡ መረጃዎችን ለትምህርት፣ ለግንዛቤ፣ ለምርምር ለሌላም ትመለከቱ ዘንድ *"ያ ትውልድ ድረ ገጽ"*ን (http://www.yatewlid.org/, http://www.yatewlid.com/) እንድትጎበኙ እየጠቆምን ሲሆን፤ በተጨማሪም ይህንን ድረ ገጽ ይበልጥ ለማጎልበትና የመጀመሪያው የዲጅታል ዳታ ጎተራ (Digital Database) መሆኑን ተቀብለን በጎደለ ለመሙላት መተባበር ማለት የያ ትውልድ ሰማዕታትን ሐውልት ማጠንከር፣ የያ ትውልድን ታሪክ ማሰባሰብ፣ ከያ ትውልድ ለቀጣይ ትውልድ መረጃ ማቀበል ነውና አበክረን የሁሉንም ትብብር ዳግም እየጠየቅን ነው።

**<u>ዋቢ መረጃ፦</u>** ያትውል ድረ ገጽ የኢሕአፓ ነሐሴ 26 ቀን 1967 ዓ.ም. ፕሮግራም

(http://yatewlid.com/images/PDF/PoleticalProgram/EPRP_Program_Nehase_1967.pdf)

የያ ትውልድ ታሪክ ህያው ነው!

"ያ ትውልድ ተቋም"

ነሐሴ 28 ቀን 2013 ዓ.ም. (September 03, 2021)